# ደንብ

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS (MCPS)**
**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**

ተዛማጅ ሠነዶች/ግብአቶች፡- ACG-RB፣ BLC፣ COB-RA፣ IOE-RB፣ JFA፣ JFA-RA፣ JGA-RB፣ JGA-RC
ሃላፊነት ያለበት ጽ/ቤት፡- ዋና የአካዴሚ ሃላፊ
ዋና የሥራ ሀላፊ
የት/ቤት ድጋፍና መሻሻል ም/የበላይ ኃላፊ

## ለተለዋጭ/አማራጭ ፐሮግራሞች የምደባ ሥርአት

I. **ዓላማ**

ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች የተለዋጭ ፕሮግራም ምርጫዎችን እና የምደባ ሥርአትን ለይቶ ለመግለጽ

II. **ዳራ-ቅድመ መነሻ ምክንያት**

አማራጭ ፕሮግራሞች፡- ለመካከለኛ እና ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በመደበኛው የአካደሚክ ፕሮግራሞች ከሚገኙት በተጨማሪ የአካደሚክ፣ የስነምግባር፣ ማህበራዊና ስሜታዊ አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም ዘርፎችን-ረድፍ ለማስፋት የተነደፉ ናቸው። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አማራጭ ፕሮግራሞች ትልም፣ እውነታዎች ላይ የተመሠረተ አላማ፣ እና የሚገኙባቸው ቦታዎች፣ ከ MCPS የመካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች አጠቃላይ ፕሮግራሞች- እስከ - ሌሎች ቦታዎች ላይ ከሚገኙት የ MCPS ት/ቤቶች፣ ወይም የማህበረሰብ አጋር ኤጀንሲዎች ይለያያል።

ከሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ/"Board of Education Policy ACA" ጋር ለማጣጣም እድሎ የሌለበት፣ ፍትሃዊ/ሚዛናዊ፣ እና ባህላዊ ብቃት፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የትምህርት እድሎችን ተጠቃሚ ለመሆን እንቅፋት የሚሆኑባቸውና የሚከለክሏቸው ነገሮችን ለይቶ ማወቅ ላይ ይሠራል። ትምህርት ቤቶች አንድን ተማሪ ወደ አማራጭ ፕሮግራሞች ከማቅረብ/ከማስተላለፋቸው በፊት የተለያዩ ዓይነት የባህርይ፣ የዲስፕሊንነ የማስተማር ዘዴዎችን/ስልቶችን በተከታታይ እየቀያየሩ መሞከር እና ከተማሪው በላይ ሊያስፈልጓቸው የሚችሉ የትምህርት ድጋፎችን ወይም አገልግሎቶችን ለመለየት ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይጠበቅባቸዋል። የተለዋጭ ፕሮግራም ምደባ ልምዶች እና የስነ-ምግባር/ዲሲፕሊን ልምዶች ተከታታይ፣ አግባብነት ያላቸው፣ ተመጣጣኝ እና በተመጣጠነ ሁኔታ ተፈፃሚ መሆን አለባቸው።

III. **የሌሎች አማራጭ ፕሮግራሞች መግለጫ**

A. ደረጃ 1 አማራጭ ፕሮግራሞች በእያንዳንዱ የ MCPS መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ ይገኛሉ፣ እንዲሁም ያልተሳካላቸው ለሆኑ ተማሪዎች ቀጥተኛ የሆነ አከደሚክ ትምህርት፣ ባህሪ፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ ድጋፍ እና ትምህርት ይሰጣል፣ እና በ መደበኛ ትምህርት መርሀ ግብሮች እና የት/ቤት እንቅስቃሴዎች ተጨማሪ ድጋፍ በመስጠት በጥሩ ሁኔታ አገልግሎት ይሰጣል። ተማሪዎች በደረጃ 1 አማራጭ ፕሮግራሞች በመካከለኛ እና/ወይም በ2ኛ ደረጃ ትም/ቤት በሚቆዩበት ዓመታት ወይም ከዚያ በተያያዘ በከፊል ሊሳተፉ ይችላሉ። በእያንዳንዱ መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በትም/ቤት

ርእሰመምህር ቁጥጥር ስር ያለ የነኛ ደረጃ አማራጭ መርሃግብር ዲዛይን፣ ስልጠና፣ እና አፈፃፀም ሰራተኞች ይመደባሉ።

B. ደረጃ 2 አማራጭ ፕሮግራሞች በብሌር ጂ. ኢዊንግ (Blair G. Ewing) ማዕከል እና በመላ ካውንቲው ውስጥ ባሉ ሌሎች ቦታዎች ላይ ይገኛሉ እናም በአጠቃላይ ከሪኩለም ለመመረቅ የሚያስፈልጉ ክሬዲቶች፣ ትናንሽ የክፍል ትምህርቶችን እና ቡድኖችን በመጠቀም ግላዊ የሆኑ፣ ሁለንተናዊ-ተማሪነት (whole-student approach)፣ በተማሪ ግላዊ ሁኔታ ላይ የተቀረጸ፣ እመርታን የተላበሰ፣ ከመደበኛ የማስተማር ጥንቅር በተለየ ሁኔታ ይሰጣል።

1. የደረጃ 2 አማራጭ ፕሮግራሞች ዓላማ፡- በመደበኛ የአካዳሚክ ፕሮግራሞች ውስጥ ላልተሳካላቸው እና ትምህርታቸውን ላቋረጡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ቀጥተኛ የሆነ አካደሚክ-ትምህርት፣ ባህሪ፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ ድጋፍ ለመስጠት ነው።

2. ደረጃ 2 አማራጭ ፕሮግራሞች የአካዳሚ ትምህርት ፕሮግራም ዳግመኛ-እንዲሰማሩ የተለያዩ የአካደሚክ ትምህርት ምዝገባ መንገዶችን፣ እና የመመረቂያ መስፈርቶችን እንደ ኬዝ ማናጅመንት፣ የአውታረ-መረብ ትምህርት፣ ጣምራ ምዝገባ/ትምህርት ተለዋዋጭ የትምህርት ሠዓቶችን የሚያሠሉ በተማሪዎች ልኬት ላይ የተዘጋጁ የማስተማር እቅድ የተለያዩ አማራጮች ለእያንዳንዱ ተማሪ የትምህርት መርሃግብር የተለያዩ መንገዶችን ያቀርባል።

3. ተማሪዎች ለደረጃ 2 አማራጭ ፕሮግራሞች ለመካከለኛ ደረጃ እና/ወይም ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዓመታት ወይም እስከ ተወሰነ ክፍለ ክፍለ ጊዜ ለመመዝገብ ይችላሉ።

C. ደረጃ 3 አማራጭ ፕሮግራሞች የሚገኙት በብሌር ጂ. ኢዊንግ ማእከል (Blair G. Ewing Center) እና በካውንቲው ውስጥ ባሉ ሌሎች ስፍራዎች ሲሆን፣ ልክ እንደ ደረጃ 2 አማራጭ ፕሮግራሞች አንድ ዓይነት አጠቃላይ ስርዓተ ትምህርት ያቀርባሉ። በ MCPS Regulation JGA-RB፣ እገዳ እና መባረር፣ ደረጃ 3 (ከ 11 እስከ 45 የትምህርት ቀናት ጊዜ) ወይም ለጊዜው ከትምህርት ቤት ለተባረሩ የመካከለኛና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች አማራጭ ፕሮግራሞች ተማሪዎችን ከተመሳሳይ የትምህርት አገልግሎቶች እና ተገቢውን የባህርይ የድጋፍ አገልግሎቶች በመደበኛነት ወደ መደበኛ አካዴሚያዊ መርሃግብር እንዲሸጋገሩ ያቀርባሉ

IV. **የአማራጭ ፕሮግራም ዓላማ እና አባልነት ምደባ ኮሚቴ (APAC)**

A. የባለድርሻ አካላት ኮሚቴ ግምገማዎች እና ወደ ደረጃ 2 አማራጭ ፕሮግራሞች መግቢያ ለማስተላለፍ አማራጭ ፕሮግራሞች። የኮሚቴ አባልነት የሚያካትተው (በዚህ አይወሰንም)፣ ከ.. ተወካዮች-

1. ደረጃ 2/3 አማራጭ ፕሮግራሞች ርእሰመምህራን/ተወካዮች፣

2. የዋና ሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት ዋና ኦፊሰር

3. የልዩ ትምህርት ጽ/ቤት፣ Office of Special Education

4. የት/ቤት ድጋፍ እና ማሻሻያ ጽ/ቤት እና

5. የተማሪ እና የቤተሰብ ድጋፍ እና ተሳትፎ ጽ/ቤት።

B. APAC ቢያንስ በእያንዳንዱ የማርከ መስጫ ወቅት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፣ እና እንደአስፈላጊነቱ ብዙ ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።

C. APAC ስለ ምደባ ውሳኔዎች መረጃን እና የአማራጭ ፕሮግራሞችን አፈፃፀም ለመገምገም ከቦርድ ፖሊሲ ACA ጋር፣ መድልዎ፣ እኩልነት፣ እና ባህላዊ ብቃቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ላይ ግምገማዎችን እና እንዲሁም ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ከላይ በክፍል III.AC ውስጥ ባሉት ቅደም ተከተሎች መሠረት ይገመግማል።

V. **ስርዐተ ሒደት**

A. Level 1 Alternative Programs-ደረጃ 1 አማራጭ ፕሮግራሞች

1. አንድን ተማሪ ወደ ደረጃ 1 አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም ከማስተላለፍ አስቀድሞ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ የተመሰረተ የትምህርት ማኔጅመንት ቡድን (EMT) ከመደበኛው የትምህርት ፕሮግራም ውስጥ ማንኛውም የታዘዙ መመሪያዎች እና/ወይም የባህሪ ጣልቃ ገብነት ስትራቴጂዎች በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በተከታታይ መሰጠቱን የመገምገም ሃላፊነት አለበት። ተማሪው(ዋ) በእንደዚህ ዓይነት ጣልቃገብነቶች እና ስትራቴጂዎች ላይ ግስጋሴ-ለውጥ ካላሳየ(ች)፣ የ EMT ቡድን ተማሪው(ዋ) ከደረጃ 1 አማራጭ ፕሮግራሞች ተጠቃሚ መሆን ይችል/ትችል እንደሆነ መወሰን ይችላል።

   a) እንደአግባብነቱ ወላጅ/አሳዳጊ እና መስፈርቱን የሚያሟላ/የምታሟላ ተማሪ የ EMT ስብሰባ እንደሚደረግ እንዲያውቁት እና በስብሰባው እንዲሳተፉ እና ግብረ-መልስ በሚሰጡበት ጊዜ እንዲሆን ለማድረግ በተቻለ መጠን ጥረት መደረግ አለበት።

   b) የ EMT ቡድን መረጃዎችን ከተለያዩ ምንጮች ማግኘት አለበት፣ ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፣ ነገር ግን በነዚህ መረጃዎች ያልተገደቡ ናቸው።

      (1) በ MCPS Form 272-9 ላይ የተሰጠ መረጃ/ኢንፎርሜሽን፣ ከመምህር (ት) የተሰጠ መረጃ፣ እና MCPS Form 272-10፣ የጣልቃገብነት ሠነዶች

      (2) የተሳትፎ ውሂብ

      (3) የምዝገባ ውሂብ፣ የሪፖርት ካርዶችን ጨምሮ

      (4) የተሰጡ አስተያየቶች የፅሁፍ ወይም የቃል ሪፖርቶች

      (5) የጤና መዝገብ

      (6) የሕክምና፣የሥነ ልቦና፣ የሥነ-አእምሮ፣ እና/ወይም የእድገት (አስተዳደግ) ሪፖርቶች

      (7) የመላመድ/የመስማማት ባህርይ ግምገማ፣ የ MCPS ቅጽ 336-64 መሙላትን ያካትታል፣ ተግባራዊ የስነምግባር ግምገማ (FBA)፣ እና MCPS Form 336-65፣ የስነምግባር ጣልቃ ገብነት እቅድ (BIP)

      (8) ቀደም ሲል ጣልቃ በመግባት የተተገበሩትን እርምጃዎች እና እርምጃዎቹ ለውጥ አላስገኙም የሚሉ የ FBA እና የ BIP መረጃ ሰነዶች

9 የቀድሞው EMT ስብሰባ ውጤቶች

2. EMT መመሥረት ያለበት-

a) በደረጃ 1 አማራጭ መርሃግብር (ግስጋሴ) የተማሪውን ለመገምገም በተማሪው ፍላጎቶች ላይ በመመርኮዝ፣ አካዴሚያዊ፣ ባህሪ፣ ማህበራዊ፣ እና/ወይም ስሜታዊ መስፈርቶች፣

b) የጣልቃ ገብነትን ውጤታማነት ለመወሰን ተማሪው በደረጃ 1 አማራጭ ፕሮግራም ውስጥ እንዲቆይ የሚጠበቅበት ያክል ጊዜ፣ እና

c) ለመደበኛ ግምገማዎች እና ለማስተካከል-ለማሻሻል የሚያስፈልገው የጊዜ መጠን እንደአስፈላጊነቱ፣ መወሰድ ያለባቸው ግቦች።

d) ተማሪዎች ቢያንስ አንድ የማርክ መስጫ ክፍልጊዜ እስከሚጠናቀቅ ድረስ (በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የሚገኙ ተማሪዎች ) ወይም አንድ ሴሚስተር (የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች) በአንድ ፕሮግራም ውስጥ እንዲቆዩ ይጠበቅባቸዋል።

e) ቢያንስ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በእያንዳንዱ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ መገምገም አለባቸው እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በየሴሚስተሩ መገምገም አሁባቸው።

3. በ EMT አስተያየት መሰረት፣ እና በወላጅ/ሞግዚት እና ብቁ የሆነ ተማሪ እንደአስፈላጊነቱ፣ተማሪው(ዋ) ወደ ደረጃ 1 አማራጭ ፕሮግራም ይመደባል/ትመደባለች። አገልግሎቶቹ በአስቸኳይ ጊዜ ወይም ተፈጥሯዊ የሽግግር ክፍተት በሚጀምርበት ወቅት፣ እንደ የማርክ መስጫ ወቅት መጨረሻ ላይ ይጀመራሉ።

4. ተማሪው(ዋ) በደረጃ 1 አማራጭ ፕሮግራም ውስጥ በሚገኝበት/በምትገኝበት ወቅት-

a) የታቀደ ጣልቃ ገብነት በተከታታይ ሥራ ላይ መዋል እና በሰነድ መያዝ አለበት።

b) የትምህርት ቤቱ EMT በየደረጃው የሚፈጠሩ ተፅእኖዎችን ለመከታተል እና ለመገምገም መደበኛ ስብሰባዎችን ያካሄዳል። ቡድኑ ከላይ የተጠቀሱትን የተፃፉ ዶኩሜንቶች መገምገም አለበት እና በደረጃ 1 የአማራጭ ፕሮግራም አስተማሪ እና በመደበኛ የአካዳሚ ፕሮግራም መምህራን መካከል ምክክር ማድረግ አለበት።

5. በፕሮግራሙ ውስጥ ቀጣይ ተሳትፎ የሚወሰነው በ EMT ሲሆን ከወላጆች/አሳዳጊዎች፣ መስፈርት ከሚያሟላ/ከምታሟላ ተማሪ ግብዓት በመውሰድ ነው።

6. ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሚገቡ የመካከለኛ ደረጃ ተማሪዎች፣ EMT ከእያንዳንዱ ት/ቤት ደረጃ 1 የአማራጭ ፕሮግራም ተወካዮች፣ እና የወላጅ/አሳዳጊዎች፣ እና ተማሪዎችን እንደአግባብነቱ ያቀፈ ኮሚቴ፣ ተማሪዎቹ ወደ ሚቀጥለው የት/ቤት ደረጃ እንዲሸጋገሩ ለማቀድ ይሰበሰባሉ።

7. ደረጃ 1 አማራጭ ፕሮግራሞች በእያንዳንዱ ት/ቤት የርእሰመምህሩ(ሯ) ሃላፊነት ነው፣ እናም በት/ቤት ድጋፍና መሻሻል ጽ/ቤት ድጋፍ እና ቁጥጥር ይደረጋል።

B. ደረጃ 2 አማራጭ ፕሮግራሞች

1. በደረጃ 1 አማራጭ ፕሮግራሞች በት/ቤት ከተሰጠው መደበኛ የትምህርት ፕሮግራም ተጨማሪ ድጋፍ እንደ ሪሶርስ መማሪያ ክፍል የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ወይም ሌሎች የተዋቀሩ ጥንቅሮች፣ ወደ ደረጃ 2 አማራጭ ፕሮግራሞች ማስተላለፍ ይቻላል።

2. ተማሪን ወደ ደረጃ 2 አማራጭ ፕሮግራም ከማስተላለፍ አስቀድሞ፣ የሚያስተላልፈው ትምህርት ቤት EMT፣ የተማሪ ሰራተኛን ጨምሮ (PPW) ጨምሮ፣ ማንኛውም የታዘዙ መመሪያዎች እና/ወይም የባህሪ ጣልቃ ገብነት ስትራቴጂዎች ወይም እንደ መርጃ መሣሪያ ያሉ ሌሎች የተዋቀሩ ጥንቅሮች በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ በደረጃ 1 ላይ አማራጭ ፕሮግራም በተከታታይ መሰጠቱን የመወሰን ሃላፊነት ይወስዳል። ተማሪው(ዋ) በእንደዚህ ዓይነት ጣልቃገብነቶች እና ስትራቴጂዎች ላይ ግስጋሴ-ለውጥ ካላሳየ(ች)፣ EMT ተማሪው(ዋ) ከደረጃ 2 አማራጭ ፕሮግራም ለመጠቀም እንደሚችል/እንደምትችል እና ከተፈለገ ተጨማሪ ድጋፍ እንደሚያስፈልገው/እንደሚያስፈልጋት ይወስናል።

   a) ወላጅ/አሳዳጊ እና መስፈርቱን ለሚያሟሉ ተማሪዎች እንደአግባብነቱ ስለ EMT ስብሰባ እንዲያውቁት እና ስብሰባውን ለመሣተፍ እና አስተዋጽኦ ለማድረግ በሚችሉበት ጊዜ ቀጠሮ ለማድረግ የተቻለ ጥረት መድረግ አለበት።

   b) EMT ከተለያዩ ምንጮች መረጃዎችን ማግኘት አለበት፣ ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፣ ነገር ግን በነዚህ ብቻ አይገደብም፦

      (1) በ MCPS Form 272-9፣ መምህር ያስተላለፈ(ች)ው፣ እና MCPS Form 272-10፣ ጣልቃ-ገብ የተደረገባቸው ሠነዶች

      (2) የተሳትፎ ውሂብ

      (3) የምዝገባ ውሂብ፣ የሪፖርት ካርዶችን ጨምሮ

      (4) የተደረጉ ግንዛቤዎችን/አስተያየቶችን የፅሁፍ ወይም የቃል ሪፖርቶች

      (5) የጤና መዝገብ

      (6) የሕክምና፣ የሥነ ልቦና፣ የሥነ-አእምሮ እና/ወይም የእድገት ሪፖርቶች

      (7) የ MCPS ቅጽ 336-64፣ ተግባራዊ የስነምግባር ምዘና (FBA)፣ እና MCPS ቅጽ 336-65፣ የስነምግባር ጣልቃ ገብ እቅድ (BIP)

      (8) ቀደም ሲል ጣልቃ በመግባት የተተገበሩትን እርምጃዎች እና ለውጥ አላመጡም የሚባሉ የ FBA እና የ BIP መረጃ/ሰነዶች

      (9) የ EMT የቀድሞ ስብሰባዎች ውጤቶች

(10) በጣልቃ-ገብ ዕቅዶች ላይ የተጠቆሙ ለውጦች

(11) እንደአግባቡ እንዲተገበሩ አስተያየት የተሰጠ የማስተማሪያ ስልቶች

3. የ EMT ቡድን ተማሪውን ወደ ደረጃ 2 አማራጭ ፕሮግራሞች ከመራ፣ የ MCPS ቅጽ 336-55፣ የአማራጭ ፕሮግራም ምደባ፣ ተሞልቶ ተማሪው(ተማሪዋ) ከሚላክበት/ከምትላክበት ትምህርት ቤት ርእሰመምህር(መምህርት)፣ እንደአስፈላጊነቱ፣ PPW፣ ወላጅ/አሳዳጊ፣ እና መስፈርቱን የሚያሟላ/የምታሟላ ተማሪ መፈረም አለበት።

a) በ EMT ስብሰባ ላይ የሚሣተፍ PPW፣ እንደአስፈላጊነቱ በስብሰባ ላይ ያልተገኙትን ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ብቃት ያለው/ያላት ተማሪ ስምምነታቸውን እንዲገልጹ ለመጠየቅ ይችላሉ።

b) PPW የተመራበትን የተጠናቀረ ፋይል በ APAC እንዲገመገም ለአማራጭ ፕሮግራሞች ተቆጣጣሪ ያቀርባል/ታቀርባለች።

4. APAC ሲያፀድቅ፣ ተማሪው(ዋ) ወደ ደረጃ 2 አማራጭ ፕሮግራም ይመደባል/ትመደባለች።

5. የመጓጓዣ ሁኔታ እንደተመቻቸ፣ ወደ "Level 2 Alternative Program" የተመደበ/ች ተማሪ በተቻለ ፍጥነት ወይም በመደበኛው የሽግግር ክፍተት እንደሚጀምር/እንደምትጀምር ይጠበቃል፣ በመግቢያ ስብሰባ ላይ በሚወሰነው መሠረት በማርክ መስጫ ክፍለጊዜ ማጠናቀቂያ ላይ።

6. ለእያንዳንዱ(ዷ) ወደ ደረጃ 2 አማራጭ ፕሮግራም ተቀባይነት ያገኘ/ች ተማሪ፣ ብዙ-ባለድርሻ አካላት ቡድን(በዚህ አይወሰንም)፣ የደረጃ 2 አማራጭ ፕሮግራም ርእሰመምህር(ት)/ተወካይ፣ የላኪው ት/ቤት ርእሰመምህር(ት)/ተወካይ፣ PPW፣ ወላጅ/ሞግዚት፣ እና መስፈርት የሚያሟላ/የምታሟላ ተማሪ እንደአስፈላጊነቱ፣ ስለአቀባበል ስብሰባ ያደርጋሉ–

a) በተማሪው(ዋ) ፍላጎት ላይ ተመስርቶ፣ የአከደሚክ፣ ስነ-ምግባር፣ ማህበራዊ እና/ወይም ስሜታዊ መስፈርቶች፣ ደረጃ 2 ፕሮግራም ላይ የተማሪው(ዋ)ን እርምጃ ለመገምገም፣

b) የጣልቃ-ገብ አማራጭ ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ተማሪው(ዋ) በደረጃ 2 አማራጭ ፕሮግራም ላይ እንዲቆይ/እንድትቆይ የተወሰነው ምን ያክል ጊዜ እንደሆነ፣ እና

c) ለመደበኛ ግምገማዎች እና የማስተካከያ ለውጦችን ለማድረግ የጊዜ ሰሌዳና፣እንደ አስፈላጊነቱ የመቀበያ ግቦች።

d) ተማሪዎች ቢያንስ አንድ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ እስከሚጠናቀቅ ድረስ (ለመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች) ወይም አንድ ሴሚስተር (ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች) በፕሮግራሙ ውስጥ እንዲቆዩ ይጠበቃል። ይህም፣በተማሪው(ዋ) ሪፖርት ካርድ እና/ወይም ትራንስክሪፕት ላይ የሚያገኟቸው ክሬዲቶች በትክክል ለማጠናቀቅ እድል ይሰጣል። የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ/ሴሚስተሩ ከማለቁ በፊት መልቀቅ በደረጃ 2 አማራጭ ፕሮግራም ላይ እያለ/እያለች ያገኘውን/ያገኘችውን ክሬዲት ሊያሰናክል ይችላል።

e) ቢያንስ፤ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በእያንዳንዱ የማርክ መስጫ ወቅት መገምገም አለባቸው፣ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በየሴሚስተሩ

መገምገም አለባቸው።

7. ሆኖም ግን፤ በደረጃ 2 አማራጭ ፕሮግራም መሳተፍ የዓላማውን ግቦች የማይሳካበት/ውጤት የማይገኝበት ጊዜ ይኖራል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ የአማራጭ ፕሮግራም ሰራተኞች EMT ስበሰባ፣ ወላጆች/ሞግዚቶች እና መስፈርት የሚያሟሉ ተማሪዎች (እንደአስፈላጊነቱ)፣ከሚያስተላልፈው ትምህርት ቤት የሥራ ባልደረቦች፣ ከማዕከላዊ ጽ/ቤት ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች፣ እና የተቀባዩ ትምህርት ቤት PPW ተገቢውን ቀጣይ እርምጃዎችን ለመወሰን ስብሰባ ያደርጋሉ።

8. የተማሪ እና የቤተሰብ ድጋፍና ተሳትፎ ጽ/ቤት court liaison ስፔሻሊስት ተማሪዎች ከእስር በኋላ ወደ MCPS እንዲመለሱ እና ለወላጆች/ሞግዜቶች፣ እና እንደአግባቡ ብቃት ያለው/ያላቸው ተማሪዎች ተማሪ ወደ ደረጃ 2 አማራጭ ፕሮግራም የመግባት አማራጭ ከመደበኛ አሠራር በተለየ ሁኔታ court liaison ስፔሻሊስት ኃላፊነት አለበት።

C. ደረጃ 3 አማራጭ ፕሮግራም

1. የዋና የሥራ ኃላፊ/ተወካይ የተራዘመ ከት/ቤት የመታገድ ወይም ወደ ደረጃ 3 አማራጭ ፕሮግራም እንዲሄድ/እንድትሄድ የተደረገ/ች ተማሪን እንዲባረር/እንድትባረር የተራዘመው ጊዜ እስከሚጠናቀቅ ድረስ Regulation JGA-RB, Suspension and Expulsion እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ተማሪን የመመደብ ሥልጣን አለው/አላት።

2. የትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ/ተወካይ ልዩ በሆኑ ሁኔታዎች ቀጥተኛ የተማሪ ምደባዎችን ወደ ደረጃ 3 አማራጭ ፕሮግራሞች የመመደብ ሥልጣን አለው/አላት።

3. ለእያንዳንዱ/ዷ ወደ ደረጃ 3 አማራጭ ፕሮግራም የተመደበ/ች ተማሪ ብዙ ባለድርሻ-አካላት ቡድን በዚህ አይገደብም፣ የደረጃ 3 አማራጭ ፕሮግራም ርእሰመምህር(ት)/ተወካይ፣ እና ተማሪው(ዋ) ከተወገደ(ች)በት መደበኛ የአካደሚክ ፕሮግራም ርእሰመምህር(ት)።

   a) በተወሰነው ጊዜ የመቀበያ ስብሰባ ያካሄዳሉ

   b) የተማሪውን/የተማሪዋን የማሻሻል ሂደት ለመከታተል እና የተማሪው/ዋ የረጅም ጊዜ እገዳ/ስንብት በተጠናቀቀ ጊዜ የተማሪው(ዋ)ን ሽግግርና ወደ መደበኛው ፕሮግራም መመለሻ እቅድ ለማዘጋጀት አልፎ አልፎ ይሰበሰባሉ።

4. ወላጆች/ሞግዚቶች ወይም መስፈርት የሚያሟሉ ተማሪዎች በደረጃ 3 አማራጭ ፕሮግራሞች ውስጥ ተሳታፊ የሆነ ተማሪ ወደ ደረጃ 2 አማራጭ ፕሮግራሞች ለመሸጋገር መምረጥ ይችላሉ።

## VI. ሌሎች አማራጭ የትምህርት ቅንብሮች/አፈፃጸሞች

A. ጊዜያዊ አማራጭ ትምህርታዊ ቅንብሮች/አፈፃፀሞች/ (IAES) ማለት ስንክልና እንዳለበ (ባ)ት ለተረጋገጠ ተማሪ ከመደበኛ የአካደሚክ ፕሮግራም በተለየ ሥፍራ ከ45 ቀናት ለማይበልጥ ጊዜ የሚደረግ ምደባ ነው።

1. የ IAES ምደባ ሥርዓቶች በ MCPS Regulation JGA-RC፣ የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች እገዳና ስንብት እና COMAR §13A.08.03.06 ላይ ተደንግጓል።

2. የ IAES ምደባዎች በልዩ ትምህርት ጽ/ቤት በተወሰነው መሠረት ደረጃ 2 ወይም ደረጃ 3 አማራጭ ፕሮግራሞች በሚሰጡ ጣቢያዎች ሊሠጡ ይችላሉ።

B. እንደአስፈላጊነቱ፣ የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ/ተወካይ የአደገኛ ዕጾች መልሶ ማገገሚያ ፕሮግራሞች ወደ MCPS የሚመለሱ ተማሪዎችን ለመደገፍ የሞዴል መልሶ የማቋቋም ፕሮግራሞች ሊያዘጋጁ ይችላሉ።

**ተዛማጅ ምንጮች፡-** የሜሪላንድ ትምህርት መምሪያ፣ §13A.08.01.11.B (2) (c) እና §13A.08.03.06.

**የደንቡ/የመመሪያው ታሪክ፡-** አዲስ ህግ፣ ነሐሴ 2 ቀን 1996፣ መስከረም 28/2007 ተሻሽሏል፣ ነሐሴ 13/2009 ተሻሽሏል፣ ጁላይ 30/2018 ተሻሽሏል።